## ሪከርዶችን ወደ ሪከርድ ማዕከል ስለማዛወር

**ቅድመ-ዝግጅት፡-**

ሪከርዶችን ወደ ሪከርድ ማዕከል ከማዛወር በፊት ዝውውሩን አመቺና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል።

**ሀ/ የዝውውር ሥራውን ማቀድና ለሥራው አመቺ ሁኔታዎች መፍጠር፡-**

- የዝውውር ሥራ የሚካሄድባቸውን ሪከርዶች መጠንና ሥራው የሚፈጀውን ጊዜና በጀት መተመን ከመ/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር የበጀት ፣ የሰው ሃይልና የሥራ ቦታና ቁሳቁሶች ወዘተ… ማዘጋጀት፣

- ሪከርዶችን የማፅዳትና፣የማናፈስ ሥራ ማከናወን፡-

የሚዛወሩ ሪከርዶች አብዛኛዉን ጊዜ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩና በጥሩ ሁኔታ ያልተቀመጡ ስለሚሆኑ በአባራ የተሸፈኑና የታመቁ በመሆናቸዉ በሰራተኞች ጤንነት ላይ ችግር ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ሪከርዶቹን ማፅዳትና ማናፈስ አስፈላጊ ነው።

**ለ/ ሪከርዶችን በየዓይነታቸው በማደራጀት መመዝገብ፡-**

- በሪከርድና ማህደር ሃላፊ ተቆጣጣሪነት የሚንቀሳቀሱትንና የማይንቀሳቀሱትን ሪከርዶች መለየት፣

ለዝውውር ስራ አመቺ እንዲሆኑ መ/ቤቱ የሥራ ሂደት የተፈጠሩትን ሪከርዶች ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱትን ሪከርዶችን በየሥራ ክፍሎቻቸው አማካይነት በመለየት ማደራጀት፤ማውጫና ማፈላለጊያ ዘዴዎቻቸውን ማካተት፣

- ምንጫቸው ያልታወቁ በእጅጉ የተመሰቃቀሉ ሪከርዶችን በተቻለ መጠን መነሻቸውን በማጥናት በተፈጠሩበት የስራ ክፍልና በጉዳይ ማደራጀት፣

- የሪከርዶችን ምዝገባ የሚከናወነዉ ፋይል በፋይል በመሆኑ በብሔራዊ ቤተመዛግብት ኤጀንሲ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ቅፅ /Inventory List/ላይ ሪከርዶቹን በተፈጠሩበት የስራ ክፍል አማካይነት በጥንቃቄ መመዝገብ/እዚህ ላይ በተለይም የፋይሉ ይዘት በሚለዉ የቅፁ ክፍል ላይ ይዘቱን ስንመዝግብ በተቻለ መጠን አሳጥሮ አጠቃላይ የፍይሉን ይዘት /Summarized Content / በሚገልፅ መልክ መሆን አለበት፣

- በውጭ ቋንቋ የተፃፉ ዶክመንቶች ሲያጋጥሙ ቋንቋውን ሊረዱ በሚችሉ ሰዎች ምዝገባውን ማከናወን።

<u>ሐ/ ስለ ሪከርድ ርክክብ አደራረግ</u>

- የሪከርድ መያዣ በማዘጋጀት በ መ/ቤቱ በአንድ ክፍል ብቻ የተፈጠሩ ወይም በሲሪየስ የተደራጁ ሪከርዶችን ማስገባት፤

- በያንዳንዱ መይዣ ውስጥ የሚገኙ ሪከርዶች በመ/ቤቱ በአንድ የስራ ክፍል ብቻ የተፈጠሩ ወይም በሲሪየስ የተደራጁ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፤

- የሪከርድ መያዣዎችንና ለእያንዳንዱ መያዣ አራት የዝወውር ቅፅ ኮፒ ማዘጋጀት፤

- ስለ መያዣዎች አስተሻሸግና ስለ ቅጹ አሞላል ከኤጀንሲው የምክር አገልግሎት መጠየቅ፤

- የዝውውር ቅጾቹ በጥንቃቄና በትክክል የተሞሉና አስፈላጊውን መረጃ ያካተቱ፤ ግልፅና ንጹህ፣ስርዝ ድልዝ የሌላቸው መሆናቸውንና በሪከርድ መያዣው ውስጥ ማሸግ፤

- በያንዳንዱ መይዣ ውስጥ የተመደቡ ሪከርዶች በአማንጪው በተሰጣቸው መለያ ቁጥር መሰረት ተራቸውን የጠበቁ፣ከብረትነክ የፀዱ መሆናቸውን፤በየፋይላቸው ውስጥ መታሰራቸውንና በሚገባ የተዘጋጁ መሆናቸውን ከዝውውሩ ቅጹ ጋር ማገናዘብ፤

- የርክክብ ጥያቄ የቀረበባቸው ሪከርዶች አካላዊ ሁኔታቸው በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኙ፣ ከፊል-ተንቀሳቃሽ የሆኑ ወይም ለዘለቄታዉ ፋይዳያላቸዉ፣ለአምጪዉ አስተዳደራዊ ጠቀሚታቸዉና የተወሰነባቸዉ የማቆያ ጊዜ ያበቃላቸዉ እና ለአገልግሎት የሚቀርቡበት ጊዜ በትክክል መጥቃስ፤

- በያንዳንዱ መያዣ ዉስጥ የተመደቡት ሪከርዶች የማስወገጃ መደብ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ይህ ሳይሆን ቢቀር በማስወገጃ መደብ መሰረት በተለያየ መያዣ ዉስጥ እንደገና እንዲመደቡ ማድረግና የዝዉዉር ቅፁንም በዚሁ መሰረት ማስተካከል፤

- በያንዳንዱ መያዣ ዉስጥ የሚገኙ ፋይሎች ያልተደባለቁና ተመሳሳይ የማስወገጃ ጊዜ እንዳላቸዉ ማረጋገጥ፤ ይህ ሳይሆን

ቢቀር ከፋይሎቹ ዉስጥ ረጅም የማስወገጃ ጊዜ በመምረጥ ለመያዣ አንድ የማስወገጃ ጊዜ መስጠት፤

- መ/ቤቶች የሪከርዶች ርክክብ እንዲፈፀም የዝዉዉር ጥያቄ ለማዕከሉ ማቅረብ፤

- ለማዕከሉ ያቀረቡት ጥያቄ ትክክለኛና አግባብነት ያለዉ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከኤጀንሲዉ መልስ መጠበቅ፤

- ጥያቄዉ ተቀባይነት ሲያገኝ ቅጾች በትክክል ተሞልተዉ አንዱን ለራሳቸዉ አስቀርተዉና ሶስቱን ከተሞሉ መያዣዎች ጋር ለኤጀንሲዉ መላክ፤

- በዝውውር ቅጾች ላይ አስፈላጊው ሌሎች መረጃዎች የሰፈረና ርክክቡን ፈፅሞ አንደኛውንም የዝውውር ቅጽ ከኤጀንሲዉ በመረከብ
  ርክክቡን መፈፀም፤